# አነጋገር ቢያምር አሚሚት ይከፋል

ከእምነት ይበልጣል (አዲስ አበባ)

ለተወደዳችሁ አዘጋጆችና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ለተነፈጋቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችሁ ስትሉ ዕውቀታችሁን ገንዘባችሁን በመልካም ስራ ላይ በማዋል የእኛ የጎስቋላዎቹና የተጨቋኞቹ ማንነት ይገለጽበት ዘንድ የመድኅን ራዲዮ ጣቢያን በመክፈት አለኝታ ለሆናችሁን ውድ የኢትዮጵያ ልጆች የእኔና የመሰል እንግልቶች ሰላምታችን ይድረሳችሁ። ስጋ ቢመቸው ሕሊና ከተጎዳ ጤናም ሰላምም የለም። ገንዘብ ተትረፍርፎ ሕንጻ ቢገነባ በውስጡ ለመኖር የመንፈስ እርካታ ካልሰጠ መጽሃፉ የተለሰነ የመቃብር ሐውልት ያለውን ከመተርጎም ሌላ የሚያስገኘው የሕሊና ፋይዳ የለውም። እውቀትም በድንቁርና መሬት ላይ ጥበብን ዘርቶ ተባብሮና ተከባብሮ የመኖርን ሰብል ካላሳጨደ መሽ በከንቱ ምሳሌን ከመተግበር በስተቀር ከማን አህሎኝ ግብዝነት ውጪ ራስንም ሌላውንም ሊጠቅም አይችልም። ማን አህሎኝ ማለት ደግሞ ተወዳዳሪ የሌለው የብቻ አርቲፊሻል ባሉን (ፊኛ) እብጠት ይሆንና በምኑም በምኑም በመነካካት የተነሳ በራስ ጊዜ ተንፍሶ መቅረትን ያስከትላል። በመተንፈሱ የተነሳ ዳግም ላያብጥ ሚሾ የማሳበጫ አየር ቢሰጡት እንኳን ከሚሸሽበት ሳይዘረጋ ቀዳዳው ሳይለጠፍ ሲሚሽሽ ዳግም ዋጋ የሌለው ቁስ ተብሎ መጣልን ያስከትላል። ይህንን ወዳቂና ግዜ የማያነሳውን መጣልን በመገንዘብ ማን አህሎኝ ከማለት ከማን እኩል ሆኜ ያነሰውን ማንነቴን ከእነማን ጋር አስተካክዬ እውቀቴም፣ ገንዘቤም፣ ሰባዊ እኔነቴም በአብሮነት ጎዳና ሊጓዝ ይችላል ብሎ በመጠየቅ ለማንነት መቆም ታላቅ ብልህነት ነው። ይህ ብልህነት መልካም ፋይዳ ስላለው የተረገጠውን፣ የተገፋውን፣ መስማት እየቻለ እንዲደነቁር የተደረገውን፤ እግዜሩ በሰጠው ብርሃን መመላለስ ሲገባው በሰው ሰራሽ ጨለማ ዓይኑ የታወረውን ህዝብ አጋሩ ልሁንለት ብሎ የህዝብን ድምጽ በመያዝ ፍሬ ሊያስጨብጥ ይችላል። በዚህ መሰረት እናንተ የመድኅን ድምፅ የራዲዮ ዝግጅት ባልደረቦችና አባላት ከአራት ዓመታት ባላነሰ ጊዜ የራዲዮ አገልግሎት ድምጽ ለተነፈገው ህዝብ መድኅን ሰለሆናችሁትና ለተገፋ ወገን መቆም ህዝባዊነት ነው ላላችሁት ድንቅ ስራ ምስጋና ይድረሳችሁ እላለሁ። የተወደዳችሁ አዘጋጆች ለጀመራችሁት ህዝባዊ አገልግሎት የተመጠነ የምስጋና ገለጻ ማድረጌ የህዝብን አስተያየት ተቀብዬ እንጂ ብቻዬን ጋልቤ የምደርስ መልእክተኛ ሆኜ አይደለም። የምታገለግሉት ወገናችሁ ይህን ያህል የማስተዋሉን ዋጋና ክብር ሰጥቷችኋልና አንድ ቀን ሁላችንም የግፋችንን ጽዋ ሰብረን የድል ዋንጫ ጨብጠን በጋራ ሀሴት እስክናደርግ ድረስ የጀመራችሁትን ታላቅ የሀገራዊና የህዝብ አለኝታነት ቀጥሉ በማለት በህዝብ ስም ህዝባዊ አደራ አቀርብላችኋለሁ። ይህን ያህል ለመልካም ስራችሁ አክብሮታዊ ሰላምታ ካቀረብኩ ወደ ነጥቤ ማለትም *"አነጋገር ቢያምርም አሚሚት ይከፋል"* በማለት ወደተነሳሁበት ጉዳይ አመራለሁ። እናንተም መሰረታዊ ሃሳቤን ስታስደናግዱልኝ እጥፍ ደስታ እንድሚሰማኝ ልሸሽግ አይቻለኝምና ጉዳዩን በዝርዝር እተነትናለሁ።

ውድ አዘጋጆች አብሮ የበላ ዛሬ ብቻውን ሊበላ መሶቡን ወደራሱ አስጠግቶ ወደ ወንበር አልባ፣ ማእድ መዘርጊያ ጠረጴዛ የለሽ ጓዳ ቢያሸሽ አትደነቁ። ይልቅስ መሶብ ይዞ በህዝብ ስም በቻውን ሊጠግብ በጠላት ወንበር አልባ ጓዳ ወደ ህዝብ አዳራሽ እንዲመለስ ለማድረግ ተጣደፈ። ያልነውን ያላችሁት በዚህች ስርጓጉጥ የሆነ መንገድ በበዛበት፤ ጥንቸልና ጓጉንቸር በየፊናቸው በሚሮጡባት፤ አንበጣ በልቶ ሳይጠግብ ማሳ ሙሉ ሰብል በሚያወድምባት፣ ከፈጣሪ ጽድቅ እየጠየቁ ለሰይጣን ሀጢያታቸውን በሚተገብሩባት፤ ዓለም ውስጥ ነውና ምድር በእሳተ ገሞራ ብትቀላ በውቂያኖስ ውሃ እንደምትጠቁር አስቡ። ወደ እኩልነት፣ ወድ ሰላም፣ ወደ ሰብዕዊነት፣ ወደ ዲሞክራሲ፣ ወደ ፍትህ አድባባይ ለመውጣት ትጉ እንጂ ጠላት በፉጨት የጠራቸው ሰዎች ተሰባስበው ከማይቀመጡበት ወንበር ላይ ልንቀመጥ ነው ብለው ጦርነትን እንዲመክትላቸው በጠሩት ህዝብ መካከል የሰላም ዘንባባችንን ትቀበለን ዘንድ እነሆ በእኛም እጅ ተይዟል ቢሉ ያ የወንበርና የዘንባባ መስዋዕታቸው ለጠላት ወያኔ ኢሃዴግ እንጂ ለህዝቡና ለእናንተ አለመሆኑን አውቃችሁ በራሳችሁ ህዝባዊ እምነት ብቻ ተንቀሳቀሱ። የጀርመን ግንብ የተናደው በመተባበርና አንድ በመሆን እንጂ በመነጣጠል አለመሆኑን እወቁ። ተነጥለን አንድ እንሆናለን ብለው የሚይዙት የገና ተስፋ አንድ ያደርገናል ብለው ቀበሮ የእንትን እንትን ይወድቅልኛል ብላ ስትከተል ዋለች እንደተባለው የጠላት ወያኔ ስልጣን ይወድቅልኛል ብለው ከአውሮፓና ከአሜሪካ በፈጣኑ አውሮፕላን መጥተው ቦሌ ወርደው፤ ሰሜን ሆቴል መግለጫ ሰጥተው ህዝቡና ተቃዋሚዎች ከጎናችን ይሰለፉ ብለው እንደ ድመት ጸጉር ለስላሳ ፖለቲካቸውን ያስተጋቡትን የአንድ ሁለቶች አካሄድ አይድነቃችሁ። ዓለም በሁለት ጎራ የማይሰለፉ ልጆች ባታፈራ ኖሮ የመምረር የመጣፈጧ ውበቷና አስቀያሚነቷ ሊገለጽ አይችልም ነበር። ውድ አዘጋጆችና የተከበራችሁ አድማጮች በሰፊው የትዝብት እንዝርት ባዳወርኩት ፖለቲካ ልቃቂት ላይ ልገልጽ የፈለኩት አንድ ሆነው አንዱ ልጅ ለአባቱ እንዳልታዘዘው መርገምት ልጅ ወደ ጠላት ካምፕ የተጓዘው ቁጥር ሁለት መድኅን ከቁጥር አንድ መድኅን ተነጥሎ ወያኔ የህዝብን የግፍ እንባ ከሚያፈስበት ሸለቆ እየተባለ ከሚጠራው አዲስ አበባ ጽህፈት ቤት መግባቱን በተመለከተ ነው። ይህን ቁጥር ሁለት መድኅን *"እንደ ሸሚዝ የሚቀያየር የፖለቲካ እምነትና አቋም"* በሚል ርዕስ ሸዋይልማ ኪዳኔ ከምድረ ጀርመን በጦቢያ መጽሄት በቅጽ 11 በቁጥር 10 እትም ላይ ያሰፈሩትን ታሪካዊ ትዝብት ስላነበብኩ እውነትና ሃሰቱን አጣጥሜ እኔም እንደኔው እይታ አስተያየት ለመስጠት ስል ነው *አነጋገር ቢያምር አሚሚት ይከፋል* በማለት የሸዋይልማን ትዝብት ለመጋራት

የተነሳሁት። ሸዋይልማ ኪዳኔ በዚህ ታሪካዊ ትዝብታቸው *“የፖለቲካ እምነታቸውን እንደፈለጉ ለመቀያየር የማይቸግራቸው አቋማቸውን በሌላው ላይ ለመጫን የማይፈሩ፣ ድርጅትን እንደ ግል ንብረት ዝቅ አድርጎ ለማየት የሚፈልጉ፤ ፖለቲከኞች ፖለቲካን ቲያትር ያስመስሉታል። አስገራሚ የሆነ የአቋም መለዋወጥ ከሚታይባቸው በተቃዋሚ የፖለቲካ ጎራ ከሚገኙ ፖለቲከኞች ውስጥ በመድኅን ፓርቲ ውስጥ አንጃ በመፍጠር የተገለሉት ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ በአሁኑ ሰአት በዋንኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።“* በሌላም በኩል ተጨማሪ ችግር የሚታይባቸው አቶ ማህሙድ አህመድ ጋስ የተባሉ የቀድሞ የአርዱፍ ዋና ጸሀፊ የነበሩት ግለሰብ ድርጅታቸውንና የድርጅቱን ደጋፊዎች ከድተው ከወያኔ አገዛዝ እውቅና አግኝተው ተለጣፊ አርዱፍ በመፍጠርና ራሳቸውን የድርጅቱ ሊቀመንበር አድርገው በመሾም የፈጸሙትን ክህደት በሰፊው ማስረጃ እያጣቀሱ አስነብበውናል። ማን ማን እንደሆነ፤ ማንም ማንንም ሊያታልል እንደማይችል፣ አታሎ እንኳን ለጊዜው የሸፍጡን ዋጋ ያገኘ ቢመስለው የሸፍጥ ዋጋ የውርደት እዳ ሆኖ ታሪክ እንደሚመዘግበው አስነብበውናልና ምስጋና ይድረሳቸው እላለሁ። ለጊዜው አርዱፍን የምመራው እኔ ንኝ ብለው ከወያኔ ሸለቆ ገብተው ህዝብ በወያኔ ግፍ እንዲያለቅስ የእንባ ከረጢት የሚያቀርቡትን አቶ ማህሙድ አህመድ ጋስን እዚሁ ምእራፍ ላይ እንተዋቸውና ሰሞኑን አዲስ አበባ ላይ የቁጥር ሁለት መድኅን ህዝባዊ ነን እሳት በትልልቁ የርእስ ማራገቢያ ንፋስ እየተቀበል ያለጊዜው ተቃጥሎ እንዳያልቅ የምሰጋለትን የኮለኔል ጎሹ ወልዴን አንጃ ቡድን ተወዳድሮ የማሸነፍን ሰማያዊ ምኞት እንቃኝ። እንደ ሸዋ ይልማ ኪዳኔ ታሪካዊ አገላለጽ የወደቀውን የስልጣን ወንበር በአሸናፊነት አንስተው ድርጅታቸውን ብቻ ሳይሆን ከሀገር ውጥተው ውጭ ሆነው ያዘው ልቀቀው ከማለት ሀገር ቤት ሆኖ ፊት ለፊት መያያዝ ይሻላል ብለን መጥተንላችኋል ስላሉን ይህ አባባል ተጨቋኝ የሆነውን የህዝብ አካሎች ነጻ ሊያወጡን መሪ መፈክራቸውን በዶክተር ሞገስ ገብረማሪያም አስይዘው በስሜን ሆቴል አዳራሽ ምታ ነጋሪት ያሉት ኮልኔል ጎሹ ወልዴ እውነት ለወያኔ እጅ አለመስጠት ይሆንን? ሸዋ ይልማ ኪዳኔ ለዚህ ጥያቄአችን ሲመልሱልን ኮልኔል ጎሹ ወልዴ ለዘጠኝ ዓመታት ያገለገሉትን የደርግ መንግስት ከድተው ድምጻቸውን ካጠፉ በኋላ የደርግ መንግስት ስርዐት መንገዳገድ ሲጀምር የቀድሞ አለቃቸው የነበሩትን ርዕሰ ብሄሩን ኮለኔል መንግስቱን በሀይለኛ ቃላቶች እየተቹ ድምጻቸውን ለጥቂት ጊዜ አጥፍተውት ወያኔ አዲስ አበባ ለመቃረብ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ሲቀሩት በኢድሀቅ በግለሰብ ደረጃ አባል የሆኑ፤ በኋላም ኢድሀቅን ለቀው ሲወጡ መድኅን አገር ወዳድ በሆኑ ኢትዮጵያውያኖች ሲመሰረት ሊቀመንበር ሆነው በመሪነት ብቅ ያሉ ናቸው ሲሉ አስነብበውናል። ሸዋ ይልማ ኪዳኔ ትዝብታቸውን በመቀጠል ከዚያም ከኢድሀቅ ጋር እንካ ሰላንቲያ ተባብለው የስድብ ትኩሳት ሲቀዘቅዝ የመድኅን ድርጅት አባላት ሳየውቁት የክተት ጥሪ አስቀርጸው አትነሳም ወይ? አሉ። ትንሽ ሰነባብተው በመድኅን ውስጥ አንጃ ፈጥረው መሪና ፕሬዝዳንት ተብለው መድኅንን በጠረኝነት እየከሰሱ ራሳቸውን የሰላም አርበኛ ብለው ወደ ፖለቲካ መድረክ ብቅ አሉ። የኮለኔል ጎሹ ወልዴ ለረዥም ጊዜ ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር ሲደራደሩበት የነበረው ጉዳይ አደባባይ ወጥቶ ሰላማዊ የሚል የትግል ሽፋን ተሰጥቶት የወያኔን አስተዳደር እውቅና በማግኘት የሚመሩት ቡድን እውቅና የማግኘቱን ሚስጢር ሸዋ ይልማ ሲነግሩን ለመጀመሪያ ጊዜ በዚሁ ራዲዮ ጣቢያ በጽሁፍ የቀረብነውን ታዛቢዎች ራሳችንን አሳምነውናል። *“ረሃብ ስንት ቀን ይፈጀል?“* ብሎ የጠየቀን ብርቅዬው የሀገራችን ልጅ ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድኅን *“ ይድረስ ለፖለቲከኛው ይድረስ ለተቃዋሚው ጓድ“* ሲል በቅኔው በጠራው ስንኙ፦

> *’ተካክደህ ስትዋሃድ ተዋህደህ ስትካካድ ፤ ከውያኔና ከሻብዕያ በለከፈህ ክፉ ልማድ ፤ ግል ጥቅም እንደጓያ እንዳይሰብርህ ፤ ቋንጃህን በመተማመን ታክመህ፣ አጠናክረው ዓላምህን፣ ሰማዕታት የሞቱለትን፣ የህዝብ ድል ሳታሸልብ፣ በስህተት የዘረኞችን ምርጫ ሳጥን ሳታደልብ አፍሪካን በአርአይነቷ ነፃ ያወጣች ኢትዮጵያ፣ በስህተት የዘረኝነት መጥረቢያ፣ ዳግመኛ ላባንዳው ጎራ እንዳትበገር እንድባሪያ፣ ለትውልድ ትንሳዔ ድል፣ በአንድነትህ የስልት ድር፣ የህዝቡን ተማጽኖ ሰምተህ ተመለስ ወደ ህብረት ክር። አይተኸዋልና በዓይንህ፣ በመራራው እድሜ ትግልህ፣ ዛሬ እድሉ እንዳያመልጥህ፣ ሀቁን እግዛብሔር ያሳይህ። ከሞት በስተቀር ከወያኔ ተስፋ አለኝ ብለህ አታፍጥጥ፣ የህዝብ ልብ አውቆልሃል እቅጬን ተናዘዝ በግልጥ።’*

ያለው ቅኝቱ ተለዋዋጭ አቋምና ባህሪ የሚታይባቸው የፖለቲካ ሰዎች ህዝብ መካከል ተሰንቅረው ’የትውልዱን ትንሳዔ’ ጠላት በቆፈረው መቃብር የሞት ሳጥን ሰርተው ጠላታችን የሞት ሳጥናችንን ጥቁር ቀለም ሲቀባው መቀቢያው ብሩሹ ሲያልቅበት አዲስ ቀለም መቀቢያ ብሩሽ ለአስከሬናቸው ሳጥን ከማቅረብ እጃቸውን ስብስበው ቢቀመጡና ያፈረሱትን የአንድነት ግንብ ምለው ቢገነቡ ስንል እኛው በነሱው ውስጥ እኛን አስገብተን መጠየቃችን አልቀረም። ገና የኮለኔል ጎሹ ወልዴ አንጃ በተወካዩ ወይም በምክር ቤቱ ሊቀመንበር በዶክተር ሞገስ እንደተገለጸው በፕሮፌሰር ስዩም ገላዬ ከሚመራው ቡድን ጋር የሰፋ ልዩነት የለንም። በሰላማዊ መንገድ መታገል አማራጭ መሆኑን በመቀበላችን እነሱን ተቃውመን ነበር። አሁን ግን በህብረቱ ውስጥ አባል ሆነው የህብረቱን አቋም በማራመዳቸው ያው እኛው ስንለው የነበረውን የተቀበሉ ስለሆነ ያለያየንን ነጥብ በማራመዳቸው በቅርቡ ወደ አንድነት እንደምንመጣ ተስፋ እናደርጋለን። እምነታችንም የጸና ነው ሲሉ ሰማናቸው። አነጋገር ቢያምር አሟሟት ይከፋል እንዳይሆን ሰው በቃሉ ይገኝ ዘንድ ተገቢ ነው። ግና ቁጥር ሁለት መድኅን ቃሉን ጠብቆ የወያኔ ገጸ በረከት አቀባይና የወያኔም የፖለቲካ ተሳታፊ አለመሆኑን በምን ያረጋግጥ ይሆን? የህ ጥያቄ በጥልቅ ግንዛቤ ተተንትኖ ለህዝብ መቅረብ አለበት። እኔም የትንተኔውን ቀጣይ ክፍል ራዲዮ ጣቢያው እድል ከሰጠኝ በቀጣይ አቀርባለሁ እስከዚያው ደህና ሁኑ።